# <u>የስድስተኛ ክፍል አማርኛ የሞዴል ፈተና መለማመጃ</u>

## <u>ጥያቄ አምስት</u>

1. **<u>ዙሪያ ገባው</u>** የሚለው ሀረግ የሚያስተላልፈው መልዕክት የቱ ነው ?

   ሀ) ዙሪያ መዞር  ለ) የሚሽከረከር  ሐ) አካባቢው  መ) የሚወጣ የሚገባ

2. በሀገራችን የሚስተዋሉ **<u>ህፀፆችን</u>** የማስተካከል ድርሻ የሁላችንም መሆን አለበት፡፡ ለተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው፡

   ሀ) ግብረ መልስ  ለ) ችግር  ሐ) ግምት  መ) ስራ

3. የቁጠባ ባህላችን የህይወት **<u>መድህን</u>** ነው ፡፡ ለተሰመረበት ቃል ፍቺ ተመሳሳይ የሚሆነው ፡

   ሀ) ዋስትና  ለ) መተማመኛ  ሐ) መዳኛ  መ) ሀ እና ለ

4. **<u>ህብር</u>** ማለት ምን ማለት ነው ፡

   ሀ) ልዩነት  ለ) አንድነት  ሐ) በግል  መ) በተናጠል

5. ልትወድቅ የደረሰች ................ ያለች ጎጆ ውስጥ ሲያጠና ያድራል፡፡

   ሀ) ጠንከር  ለ) ዘመም  ሐ) ጥልል  መ) መንገድ

6. አየለ በሰማው መረጃ **<u>ሀሳቡን ጣለ</u>** ፡፡ ለተሰመረበት ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ የሚሆነው >

   ሀ) ቸኮለ  ለ) ወደቀ  ሐ) ተረጋጋ  መ) ሁሉም

7. ከበደ በተጠየቀው ጥያቄ መሰረት **<u>ቃሉን ሰጠ፡፡</u>** ለተሰመረበት ፈሊጣዊ ንግግር ፍቺ የሚሆነው ፡

   ሀ) ዋሸ  ለ) መሰከረ  ሐ) ለመነ  መ) መልሲ የለም

8. ከሚከተሉት ቃላት አንዱ **<u>ርዕቱ</u>** ቃል ነው ፡፡

   ሀሀ) ሳለ  ለ) ፈላ  ሐ) መታ  መ) ሁሉም

9. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የደብዳቤ ክፍል ነው።

   ሀ) መግቢያ  ለ) ሃተታ  ሐ) መደምደሚያ  መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS

10. በየአለባበሶቻችን የሚለውን ሐረግ ተነጥሎ ሲፃፍ

ሀ) በ-አለባበሶቻችን ለ) በየአለባበስ-ኣችን

ሐ) በየ-አለባበስ-ኦች-ኣችን መ) በ-አለባበስ-ኦችቻችን

11. ሰላማዊነታችን

ሀ) ሰላማዊ-ነት-ኣችን ለ) ሰላም-ኣዊ-ነት-ኣችን

ሐ) ሰላማዊነት-ኣችን መ) ሰላም-ኣዊነት-ኣችን

12. የቃላዊ ግጥሞች በየትናው የቋንቋ ዘርፍ ውስጥ ይመደባሉ?

ሀ) በስነ ጥበብ ለ) በስነ ግጥም ሐ) በስነ ቃል መ) በሰዋሰው

13. የቃላዊ ግጥሞች ዋና ዋና ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው ?

ሀ) የሙሾ ቃላዊ ግጥም ለ) የልመና ቃላዊ ግጥም

ሐ) የእርሻ ቃላዊ ግጥም መ) ሁሉም

14. ቀጥሎ ከቀረቡት ሃሳቦች መካከል ስለ ቃላዊ ግጥሞች ትክክል የሆነው፡

ሀ) በአንጉርጉሮ መልክ ሊቀርቡ ይችላሉ

ለ) የተመጠኑ ግጥሞችና ሀረጋትን ይይዛሉ

ሐ) በአብዛናው በገተሩ ማህበረሰብ ይዘወተራሉ

መ) ሁሉም

15. ከቀረቡት ሀሳቦች መካከል ትክክል ያልሆነው፡

ሀ) ቃላዊ ግጥሞች የማህበረሰቡ አንጡራ ሃብቶች ናቸው

ለ) ቃላዊ ግጥሞች በአብዛኛው በገጠሩ ማህበረሰብ ይዘወተራሉ

ሐ) ቃላዊ ግጥሞች የማህበረሰቡን ስሜት ለማነቃቃት ይጠቅማሉ

መ) ቃላዊ ግጥሞች እንደ አንድ ሀብት ሊታዩ አይችሉም

LIVEWORKSHEETS

16. ቃላዊ ግጥሞችን የመጠበቅ እና ለትውልድ የማስተላለፍ ኃላፊነት የማን ነው ?

ሀ) የቤተሰብ ለ) የመምህራን

ሐ) የመንግስት መ) የሁሉም የማህበረሰብ ክፍል

17. ከቀረቡት ቃላት መካከል በፍቺ ተመሳሳይ ያልሆነው ፡



ሀ) ጎመጀ ለ) ቋመጠ ሐ) መታ መ) ጓጓ

18. **<u>ኣም</u>** የሚለውን ቅጥያ

የያዘው ቃል የትኛው ነው ?

ሀ) ድንጋያማ ለ) ተራራማ ሐ) ውሽታም መ ) ቀጫጫን

19. በአንቀፅ ውስጥ ሀይለ ቃሉ መሃል ላይ መገኘቱን የሚያሳየው የአንቀፅ ቅርፅ የቱ ነው ?

ሀ)  ለ)  **ሐ)**  መ) 

20. መሂዷ ነው መሰናበቷ ነው ፣ ይህ ቃላዊ ግጥም ............. ነው ፡፡

ሀ) የሸኝት ለ) የሙሾ ሐ) የሰርግ መ) የለቅሶ

21. **<u>ስለሀገራችን</u>** ከሚለው ቃል መድረሻ ቅጥያው፣

ሀ) ስለ ለ) እን ሐ) ኣችን መ) ራችን

እጇን አትቅበሩት ይቁም እንደ እንግዳ፣

ሸኝታበታለች ብዙ ብዙ እንግዳ፡፡

22. ይህ ግጥም ምን ዓይነት ቃላዊ ግጥም ነው ?

ሀ) ፉከራና ቀረርቶ ለ) ሙሾ

ሐ) የፍቅር ግትም መ) የሰብል ጥበቃ ግጥም

23. ነብዩ ባለፈው ዓመት የስድስተኛ ክፍል ተማሪ ነበር፡፡ የጊዜ ተውሳከ ግሱ፡

ሀ) ነብዩ ለ) ባለፈው ዓመት

ሐ) የስድስተኛ ክፍል መ) ተማሪ

LIVEWORKSHEETS

24. ድርሰት ከመፃፋችን በፊት ዋና ዋና ኃሳቦችን በቅደም ተከተል የማስቀመጥ ሂደት ምን ይባላል?

ሀ) ማርቀቅ

ለ) አንቀጽ መፃፍ

ሐ) ር ዕስ ማዘጋጀት

መ) አስተዋፅኦ መንደፍ

25. ሰለ ስነ ቃል ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ስነቃል ከመናገር ይልቅ መፃፍን ይመርታል

ለ) ስነ ቃል የአንድን ማህበረሰብ ወግ፣ እምነትና ባህል ይባላል

ሐ) ተለዋዋጭነትና ቃላዊነት የስነቃል ባህርያት ናቸው

መ) ስነቃል ህብረተሰብን ይገልፃል፣ ይመክራል ያስተምራል

ትመጫለሽ ብዬ ሳይ ማዶ ሳይ ማዶ፣

የልጅነት አይኔ ሟሟ እንደበረዶ፡፡

26. ግጥሙ ለየትኛው ቃላዊ ግጥም ሳሌ ይሆናል?

ሀ) የፍቅር

ለ) የስራ

ሐ) የልጆች ጨዋታ

መ) የልመና

27. ከሚከተሉት ስነቃሎች መካከል እንቆቅልሽ የሆነው የቱ ነው ?

ሀ) ሲከተሉት የሚርቅ ሲርቁት የሚከተል

ለ) የሚሰቀው ያጣ ሌባ ሰላማዊ ሆኖ ገባ

ሐ) ሸክላ ቢጥሉት ገለባ

መ) ሆዱን ያለ ሆዱን የወጋ

28. ከሚከተሉት ጥንድ ቃላትን ከያዙ አማራጮች መካከል ተቃራኒ ፍቺ ያላቸው ፡

ሀ) ረብሻ ፣ ብጥብጥ

ለ) ፍጅት ፣ እልቂት

ሐ) ቀልድ ፣ ቧልት

መ) ጥፋት ፣ ልማት

ፈሪ ጨነቀው ተርበደበደ፣

ጥይት ዘነበ እሳት ወረደ፣

ውረድ እንውረድ ተባባሉና፣

29. አስደበደቡት አፋፍቆሙና፡፡ የሚለው ግጥም ከሚከተሉት የስነቃል ዘርፎች መካከል ለየትኛው ተስማሚ ነው ?

ሀ) ሙሾ

ለ) ልመና

ሐ) እንጉርጉሮ

መ) ፉከራ

LIVEWORKSHEETS

30. ደብተሬ የሚለው ቃል ላይ ያለው ቅጥያ አገልግሎቱ መንደን ነው ?

ሀ) ባለቤት ማመልከት ለ) ብዛትን ማመልከት

ሐ) ጾታን ማመልከት መ) ባለንብረትን ማመልከት

31. **ደባ** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) ተንኮል ለ) ክፋት ሐ) ደግ ነት መ) ሀ እና ለ

32. ከሚከተሉት አንዱ የተፅው ኦ ስም ነው ፡፡

ሀ) ሃና ለ) በሬ ሐ) ተማሪ መ) ወንድ

33. ቂመኛ በሚለው ቃል ውስጥ ዋናው ቃል የቱ ነው ?

ሀ) ቂም ለ) ቀም ሐ) ኛኛ መ) መልስ የለም

ሀምሌ ነሀሴ ያላረሰ ሰው፣

ሞፈር ቀንበሩን ............... ፡፡

34. በባዶ ቦታው ሊገባ የሚችለው ሃረግ የትኛው ነው ?

ሀ) ጋቢ ያልብሰው ለ) ቀሚስ ያልብሰው

ሐ) ነተላ ያልብሰው መ) መልስ የለም

35. ከሚከተሉት አንዱ ስነቃል ነው ፡፡

ሀ) እንቆቅልሽ ለ) ተረት ሐ) ቃላዊ ግጥም መ) ሁሉም

36. ምዕላድ በስንት ይመደባል ?

ሀ) 2 ለ) 3 ሐ) 4 መ) 5

37. **ረብ** ለሚልው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ፡

በሙሉ ለ) ስጦታ ሐ) ጥቅም መ) ግምት

38. **ሂስ** ለሚልው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ፡

ሀ) ግምት ለ) ድርሻ ሐ) ስጦታ መ) ግምገማ

LIVEWORKSHEETS

39. **<u>በነቂስ</u>** ለሚልው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ፡

ሀ) በሙሉ ለ) በግምት ሐ) አስቸጋሪ መ) በተናጠል

40. **<u>አዳጋች</u>** ለሚልው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ፡

ሀ) ዳገት ለ) አዋሳኝ ሐ) አስቸጋሪ መ) አስቸኳይ

41. **<u>ፋንታ</u>** ለሚልው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ፡

ሀ) ድርሻ ለ) ቀላል ሐ) ድርሻ መ) ስጦታ

42. **<u>ውርስ</u>** ለሚልው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ፡

ሀ) ጥቅም ለ) ስጦታ ሐ) የቀረ መ) ሂደት

43. ሌጣ ለሚልው ቃል ተመሳሳይ የሆነው ፡

ሀ) አስቸጋሪ ለ) ብቸኛ ሐ) ያልተጫነ መ) እንግዳ

44. ከሚከተሉት መካከል ነፃ ምዕላድ የሆነው የቱ ነው

ሀ) በሬ ለ. ላሞች ሐ. ልማዳዊ መ. ልጅነት

45. "ለመነ" ብለን አለማመን ካልን "ለበሰ" ብለን _______ማለት እንችላለን።

ሀ. አለባበስ. ለ. መልበስ. ሐ. አልባሳት. መ. መልስ የለም

LIVEWORKSHEETS